# የኮሌጅ እና የሥራ
# የዕቅድ መመሪያ




የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ድስትሪክት

**ከ 6 ኛ እስከ 12 ኛ**
**ክፍሎች (2018-2019)**

Dedicated to Excellence
Cherry Creek Schools

Cherry Creek Schools
Dedicated to Excellence

To inspire every
student to think
to learn
to
achieve
to care







የተዘጋጀው  በጆይ ግርን (Joi Green )የዲስትሪክት የምክር አገልግሎት አስተባባሪ



Cherry Creek Schools

*ውድ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች እና ወላጆች*

*ለወደፊቱ ስኬታችው እንደ መንገድ ካርታ(ሮድማፕ) የምመራችሁ እዚህ አለ.*

*እያንዳንዱን ተማሪን ከወደፊት አላማው/ዋ/ስኬት ጋር ለማገነኘት ለመርዳት የተዋቀረዉን የ2018-19 የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች የኮሌጅ እና የስራ ዕቅድ መመሪያን ለመካከለኛና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሳስተዋውቅ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። በዚህ አጠቃላይ መመሪያ ዉስጥ በመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ በሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት እና ከዝያም ባሻጋር አካዳሚያዊ ጎዳናዎችን ስለማቀድ ጠቃሚ መረጃን ያገኛሉ።*

*ይህ መመሪያ ስለ እያንዳንዱ ተማሪ የግል የስኬት መንገድ ነው። ተማሪዎች የሁለት ወይም የአራት ዓመት ኮሌጅ መግባት ቢመርጡም ወይንም ወደ ስራ ልምምድ መግባት ቢፍልጉም ፤ወይንም ወታደር መሆን ቢፈልጉ ወይንም ቀጥታ ወደ ስራ አለም ለመሰማረት ብፈልጉም እንኳ የአካዳሚክ እና ፕሮፌሽናል ህልሞቻቸዉን እዉን ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎችና መረጃዎች ያገኛሉ።*

*ይህ መመሪያ የተለያየ እና ጥብቅ የሆኑ የአካዳሚክ ፕሮግራሞቻችንን፤ ት / ቤቶቻችንንና፤ ማዕከሎቻችን ላይ ያተኩራል። ስለ የምረቃ መስፈርቶች በትምህርት ቤቱ ቦርድ እና በእስቴቱ የተደነነገዉን ደንብ በዝርዝር ያስረዳል። በእነዚህ ገፆች ውስጥ፤ በዲስትሪክቱ ውስጥ ስለ አስገራሚው አዳዲስ ፈጠራዎች፤ ለምሳሌ ስለ የቼሪ ክሪክ ኢኖቬሽን ካምፓስ (CCIC)ይማራሉ። ይህንን ተቋም በ2019 ለመክፈት ዕቅድ ተይዟል እናም የ CCSD የ 2 ኛ ደረጃ ት / ቤት ተማሪዎችን ከከፍተኛ የሙያ ስልጠና እና እድሎች ጋር ለመገነኘት ተቅዶ የምወቀር ነው። በዝህ ጥራዝ ዉስጥ በድስትሪክቱ አማካሪዎች የተዘጋጁ የጊዜ ሂደቶችን እና የማጣሪያ ዝርዝር ያገኛሉ። እነዚህ ጠቃሚ መረጃዎች ስለ የኮለጅ ማመልከቻዎች ፤ ስኮላርሺፖች፤ የሙያ እና የቴክኒካዊ ስልጠና፤ የገንዘብ ድጋፍ እና ብዙ ርእሶች በተቻለ መጠን ቀላልና ግልጽ አድርጎ ለማቅረብ ተሞክሯል።*

*እነዚህ ሁሉ መረጃዎች የተቀረጹት ለእርስዎ ነው፤እና በድስትሪክቱ ውስጥ በምቆዩበት ጊዜ ሁሉ እንዲጠቀሙት አበረታታለሁ። በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች፤ እያንዳንዱ ተማሪ ለወደፊቱ ስኬታቸው ከሁሉ የተሻለውን መንገድ ለመገንባት የሚያስችላቸውን እያንዳንዱን መሳሪያ/መረጃ መያዙን ማረጋገጥ እንፈልጋለን። በዚህ ጉዞ ላይ እርስዎን ለማገዝ አስተማሪዎችዎ፤አማካሪዎችዎ እና የትምህርት ቤት ማህበረሰቦችዎ ዝግጁ ነቸው።.*

ዶ/ር ስካት ስግፍርድ(Dr. Scott Siegfried)

# የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቦርድ



**L-R: Karen Fisher, Dave Willman, Kelly Bates, Eric Parish, Janice McDonald**

## ራዕያችን

**የላቀ የትምህርት ድስትሪክት**

## ተልኳችን

**እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያስብ፤ እንድማር እንድከነወንለት ፤ ደንታ ያለው እንድሆን/እንድትሆን ማነሳሳት**

## እሴቶቻችን

- ስለ ተማሪዎቻችን ፍላጎቶችና ደህንነት ከሁሉም በላይ ቅድሚያ መስጠት
- ለመማር ማስተማር ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቾት ሰጪ አከባቢዎችን ማቅረብ.
- ለእያንዳንዱ ተማሪ እድገት እና ክንውን ከፍተኛ ግምት መስጠት
- ከተማሪዎችና ከቤተሰቦች ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት መፍጠር.
- የምናገለግላቸውን ተማሪዎችና ቤተሰቦች ስብጥርን/ልዩነትን ማክበር እና መረዳት

ተማሪዎችን፤ወላጆችን እና የማህበረሰብ አባላትን በትምህርት ሂደት ውስጥ እንደ አጋርነት ማሳተፍ.

- ተሳትፎን እና ስልጣንን ማበረታታት.
- የማኅበረሰቦቻችንን ስብጥር የሚያንፀባርቁና ለወጣቶች በጥልቅ የሚያስቡ ጥራት ያላቸው ሰራተኞች መሳተፍ/ መቅጠር
- ለተማሪዎችና ለወላጆች ጠንካራ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሳየት.
- ራዕይያችንን ለማሳካት ፈጠራን ማበረታታት
- ድስትርክቱን ያለማቋረጥ ማሻሻል.
- የተማሪዎችን የዕድሜ ልክ ትምህርት, ስኬት እና ሌሎችን የማገልገል ፍላጎትን ማሳደግ.



# የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት የኮሌጅ እና የሥራ  እቅድ ማውጫ መመሪያ

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት እያንዳንዱን ተማሪ ለኮሌጅ እና ለስራ ለመዘጋጀት በትጋት ይሰራል ። ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ እና ለከዚያም በኋላ በምያቅዱበት ወቅት  ፍላጎቶችዎን ለመመርመር ፤ምኞቶቻችሁን ለመከታተል እና የፈጠራ ችሎታዎችዎን ለመቀጣጣል/ለመነሳሳት  እንድችሉ በርካታ መንገዶችን እናቀርባለን. ይህ የእቅድ መመሪያ ከመለስተኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምረቃ መስፈርቶችን ለማሟላት እና ለወደፊቱ ለሚቀጥሉት አስፈላጊ እርምጃዎች እቅድ ለማውጣት በሚረዱት ሂደቶች ውስጥ አንተን/አንችን ለማገዝ/ለመርዳት  ተዘጋጅቷል.. እባክዎን እንደ  ቤተሰብ ለመነገር  ጊዜ ይመድቡ እና በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተካተቱትን መሳሪያዎች/መረጃዎች ለዉይይታችው  መሠረት  አድርገው ይጠቀሙ.

## ማዉጫ


| | |
|---|---|
| የዋና ተቆጣጣሪ መልእክት | ገጽ 3 |
| በርካታ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች | ገጽ 6 |
| የሙያ እና ቴክኒካዊ ትምህርቶች ኮርሶች | ገጽ 8 |
| የቼሪ ክሪክ ኢኖቬሽን ካምፓስ | ገጽ 9 |
| የመካከለኛ ደረጃ ት / ቤት ፕላን እና አስፈላጊነት | ገጽ 10 |
| የማቀጃ መሣርያዎች | ገጽ 12 |
| ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ሽግግር | ገጽ 13 |
| የምረቃ መስፈርቶች | ገጽ 14 |
| ለመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ዕቅድ ማዉጫ | ገጽ 16 |
| ለዕጩ  ተመራቂ ተማሪዎች  የእቅድ ማዉጫ(  2019 and 2020) | ገጽ 17 |
| ለ2021ና ዕጩ  ተመራቂ ተማሪዎችና ከዝያም ባሻጋር    የእቅድ ማዉጫ ደብተር | ገጽ 18 |
| የአንድ ወይንም ከዝያ በላይ የቋንቋ ችሎታ(Seal of Biliteracy) | ገጽ 19 |
| ሁሉንም ተማሪዎች ማዘጋጀት | ገጽ 20 |
| የኮሎራዶ የአራት ዓመት ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች የመግቢያ መስፈርቶች | ገጽ 21 |
| የመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ት / ቤቶች ግምገማዎች እና ቅድመ-ኮሌጅ ፈተናዎች | ገጽ 22 |
| የኮሌጅ ዕቅድ ማውጫ ጊዜ | ገጽ 23 |
| የገንዘብ ድጎማ (ፋይናንሻል ኤይድ) | ገጽ 24 |
| የማመካር አገልግሎት | ገጽ 25 |
| የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶቻችን ምደባ | ገጽ 26 |
| የድስትርክቱ ቢሮዎች አድራሻ/ስልክ ቁጥር | ገጽ 27 |

# በርካታ የትምህርት ፕሮግራሞች

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ስኬታማ እንድትሆን/ኝ የሚረዱ በርካታ የኮሌጅ እና የሙያ /የስራ ፕሮግራሞችን ያቀርባል። በርካታ የትምህርት ፕሮግራሞች የተለያዩ ኮርሶችንና እና የመማር ተሞክሮዎችን ያቀርባሉ። ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ የሚያስፋልጋቸዉን ነጥብና እንደዝሁም ከዚያም በሃላ ለለው ለከፍተኛ ትምህርት ስኬት ለማዘገጀት ከተለምዷዊ የኮርስ ቅደም ተከተል ውጪ ለተማሪዎች ዕድሎችን ያቀርባሉ።
እያንዳንዱ ፕሮግራም ግልጽ ነው እንደዝሁም በእያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት ፍላጎትና ልዩ መሻት መሰረት እያንዳንዱ ተማሪ ልታገኘው/ያገኘው/ የምችለው ነው።

ተማሪዎች ለበርካታ አመታት ትምህርታቸዉን ከተከታታሉ በሃላ ለተለያየ የድህረ ሁለተኛ ትምህርት አማራጮች ዝግጁ በመሆን ይመረቃሉ። እነዝህም የሁለት ወይንም የ4 አመት የኮሌጅ ትምህርት፤ የምስክር ወረቀት፤ የሥራ ላይ ልምምድ፤ የውትድርና አገልግሎት ወይም መደበኛ የስራ ስልጠናዎች ናቸው። በእነዚህ የኮሌጅና የሙያ ትምህርት ፕሮግራሞች ተማሪዎች ለአንዱ ወይንም ከሁለት ለአንዱ ሳይሆን ለሁለቱም አማራጮች ዝግጁ ይሆናሉ።

| ፕሮግራሞች | ገለጻ |
|---|---|
| AVID Decades of College Dreams | **AVID** የምባለው ፕሮግራም በተማሪው/ዋ የግል ጥረት አማካይነት የምገኝ ስኬት ስሆን ጠንካራ የኮሌጅ ዝግጅት ፕሮግራም ነው።AVID የምባለው ፕሮግራም እንደ ወሳኝ አስተሳሰብ፤ ኮሌጅ እና ሥራ፤ ማንበብና መጻፍ እና ሂሳብ ባሉ ትምህርቶች ውስጥ የተማሪን ስኬት የሚደግፉ በጥናት ላይ የተመሠረተ ስርዓተ-ትምህርት እና ስልቶችን ይጠቀማል። |
| AP CollegeBoard Advanced Placement Program | **Advanced Placement (AP)** አድቫንስድ ፕለስመንት **(AP)** የምባለው ተማሪዎች የተራቀቁ/ የላቁና ከፍተኛ ደረጃ ኮርሶችን ወይንም የኮሌጅ ደረጃ ኮርሶችን እንዲወስዱ ያስችላቸዋል። ከጠንካራ ኮርሶች በተጨማሪ ተማሪዎች የኮርስ ማጠቃለያ ፈተና ይወስዳሉ። ተማሪዎች የኮሌጅ ነጥብ ( ክሬድት) ለማግኘት የሚያስፈልጉትን የፈተና ውጤቶችን መስፈርቶችን በተመለከተ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ ፖሊሲዎች አሏቸው። |
| International Baccalaureate | **International Baccalaureate (IB)** እንተርናሽናል ባካሎሬት (IB) የምባለው ፕሮግራም የላቀ እውቀት እና ጥልቅ ዕውቀት ያላቸውን ተማሪዎች - በአካል፤ በአእምሮ፤በስሜት እና በስነምግባር ለማጎልበት የተለመ ነው።ፕሮግራሙ ስድስት ዋና ዋና ኮርሶችንና እንደዝሁም ተማሪዎች ከሌሎች አለማቀፍ ከሆኑት ሰዎች ጋር መግባባት እንድችሉ በራስ መተማማንና የፈጠራ ፍሎታቻዉንም ለማበረታታት የዕዉቀት ንድፈ አሳብንም ያካትታል። |
| CareerWise Colorado Tomorrow's Talent Today | **CareerWise Colorado** CareerWise ኮላራዶ የምበለው ድርጅት ከCCSD ጋር በመተባበር ለ11ኛና የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች ገና በመደበኛ ትምህርት ቤት እያሉ የስራ ልምምድ እንድያገኙ በርካታ ዕድሎችን ያመቻቹላቸዋል። የስዊስን ትምህርት ሞዴል ተከትሎ የተመሰረተው ይህ ጠንካራ የንግድ ስራ ሞዴል ተነሳሽነት ተማሪዎችን ለእውነተኛው ዓለም ኢንዱስትሪ ፍላጎቶች ዝግጁ ያደርጋል። |
| COLLEGE BOUND | **Concurrent Enrollment (CE)** ከኮሎራዶ ኮሌጅ ሲስተም ጋር በመተባበር የ2ኛ ደረጃ ት / ቤት ተማሪዎች የኮሌጅ ክሬዲት ለማግኘት የኮሌጅ-ደረጃ ኮርሶችን የመውሰድ አማራጮች አላቸው። ተማሪዎች በምወስዷቸው ኮርሶች C ወይም የተሻለ ነጥብ ቢያገኙ በኮሎራዶ ባሉት የ4 አመት የሕዝብ ኮሌጆች ዉስጥ ዉጤቱ ተቀባይነት ይኖራቸዋል ። |

| ፕሮግራሞች | መግለጫ |
|---|---|
| ASCENT | **ASCENT** የምባለው ፕሮግራም  በሁለተኛ ደረጃ መጠነቀቅያ አመት ላይ ለተማሪዎች አምስተኛ አመት በመጨመር ተማሪዎች  የኮሌጅ ኮርሶችን እንደወስዱ የምያደረግ ፕሮግራም ነው  ። በዝህ ፕሮግራም ለመሳተፍ የምፈልጉ ተማሪዎች በአማካሪዎቻቸው በኩል ማመልከት አለባችው እንደዝሁም ለፕሮግራሙ የምያስፈልጉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።የASCENT የገንዘብ ድጎማ በእስቴቱ  ዓመታዊ የበጀት  ድልድል ላይ የተመሰረተ ነው። |
| ONLINE LE@RNING Cherry Creek Schools | **( የኦንላይን ላይ ትምህርት)** የድስትሪክቱ የኦንላይን  ላይ የመማሪያ ፕሮግራም ተማሪዎች በማንኛውም ሰዓት፤ ከማንኛውም ቦታ ለመማር ምቹ የሆነ ሁኔታን  ያመቻቻል።  ኮርሶቹ በመስፈርቶች ላይ  የተመሰረቱ እና አወያይ  ናቸው።የኦንላይን  ላይ ትምህርት ተማሪዎች የምረቃ መስፈርቶችን እንድያሟሉ  ይረዳሉ። |
| CTE Career & Technical Education Your life, your world, your future. | **የሙያ እና ቴክኒካዊ ትምህርት** የሙያ እና የቴክኒካዊ ትምህርት ተማሪዎች  በኢንዱስትሪ ዕዉቅና  ያለችዉን  የምስክር  ወረቀቶችን  እና  ወይም  የኮንከረንት  ክሬዲት የሚያገኙባቸውን መንገዶች ያቀርባል።.<br><br>* ለተጨማሪ መረጃ በዚህ ጥራዝ ውስጥ ገጽ 8ን ይመልከቱ. |
| ENDEAVOR ACADEMY | **Endeavor Academy** የእንድቬየር ትምህርት ቤት እራሱን የቻለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመሆኑም ባሻጋር በድስትርክቱ ላሉት  ተማሪዎች ሁሉ ዉጤታቸዉን/ነጥባቸዉን  እንድያሻሽሉም የማታ ክፍለጊዜ የትምህርት እድልንም ይሰጣል ። |



# የሙያ እና ቴክኒክ ትምህርቶች ኮርሶች

የሙያ እና የቴክኒካዊ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተማሩትን ማሳየት የሚችሉበት እና እንዲሁም በእንዱስትሪ ደረጃ ዕውቅና ያለዉን ሰርተፍኬቶችን ወይንም የኮንከረንት እንሮልመንትን ክሬዲት/ነጥቦችን ለማግኘት የምያስችለዉን ኮርሶችን አወቅሯል እንደዝሁም መንገዶችንም አመቻችቷል።

.ስለ የ CTE አቅርቦቶች የበለጠ ለማወቅ አማካሪዎን ያነጋግሩ ወይንም ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ።

www.cherrycreekschools.org/CTE.

## በሌሎች ቦታዎች የምሰጡ የCTE ኮርሶች

*ተማሪዎች የራሳቸው መጓጓዣ ልኖራቸው ይገባል*

## በድስትርክቱ ዉስጥ የምሰጡ የCTE ኮርሶች

### የCHERRY CREEK ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የCTE ኮርሶች

- የህክምና ሙያዎች

### የCHEROKEE TRAIL ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የCTE ኮርሶች

- የወንጀል ፍትህ( CE)
- ስራ ዳሳሳ(ሰለ ስራ ጥናት ማድረግ)

### የEAGLECREST ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የCTE ኮርሶች

- የስራ ዳሳሳ( ሰለ ስራ ጥናት ማድረግ)

### የGRANDVIEW ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የCTE ኮርሶች

- የበረራ ስልጠና
- የበረራ ቴክኖሎጅ
- ● የወንጀል ፍትህ (CE)
- የምግብ ማብሰል ሙያ 1 & 2 (CE)

### የOVERLAND ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ CTE ኮርሶች

- የበረራ ስልጠና
- የበረራ ቴክኖሎጅ
- የወንጀል ፍትህ (CE)
- የህክምና ሙያዎች
- የጤና መርሆዎች (CE)
- ከፍተኛ የጤና ሳይንስ (CE)
- የነርስ ረዳት(ጤና ረዳት)
- የአውቶሞቢል ቴክኖሎጂ
- ዕጩ መምህራን (CE)

### የSMOKY HILL ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የCTE ኮርሶች

- የአውቶሞቢል ቴክኖሎጂ (CE)
- የስራ ዳሳሳ( ሰለ ስራ ጥናት ማድረግ)
- የህክምና ሙያዎች (CE)
- የምግብ ዝግጅት ና ሆቴል አስተዳዳር ሙያ 1 & 2 (CE)
- የግንባታ ሙያ 1 & 2

### የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ቤት

- የወንጀል ፍትህ (CE)
- የፎቶግራፍ ስነጥበብ (CE)
- ● ዲጂታል ፎቶ
- ከፍተኛ የሥራ ልምምድ

## ከዲስትሪክቱ ዉጪ የምሰጡ የCTE ኮርሶች

| AMES | MSU | PICKENS | | |
|---|---|---|---|---|
| ■ የጤና ሳይንስ (CE)<br>■ ፋሽን<br>■ የቅድመ መደበኛ ትምህርትቤት ትምህርት | ■ የአቪዬሽን መሰረታዊ ነገሮች (CE) | ■ የመኪና ግጭት ጥገና (CE)<br>■ ■ የኮምፒተር ጥገና (CE)<br>■ ድገዝል (CE)<br>■ ■ አጠቃላይ ኤሌክትሮኒክስ (CE) | ■ ሞባይል አፕስ (CE)<br>■ የተራቀቁ ማሽኖች (CE)<br>■ የንብረት ጥገና/እንክብካቤ (CE) | ■ የመኪነ ስፖርት ት (CE)<br>■ ብየዳ (CE) |



# የቼሪ ክሪክ ኢኖቬሽን ካምፓስ (CCIC)

የቼሪ ክሪክ ኢኖቬሽን ካምፓስ እራሱን ችሎ የምንቀሳቀስ የኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት ማዕከል ስሆን በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ተማሪዎች በሙሉ ክፍት ነው። ስርአተ ትምህርቱ በገሃዱ ዓለም እውቀቶችና ብዙ ዘርፍ በለቸው የንግድ ሰርቲፊኬቶች ላይ የተመሰረተ ስሆን እነዝህም የኮምፕዩተር ሳይንስ፤ እስከ ኤቪዬሽንና እስከ ጤና ሳይንስ ድረስ ያጠቃልላል። ይህ ተቋም አድስና ፈር ቀዳጅ የሆነ ስኬታማ የስራ መስክ ድልድይ ለተማሪዎች ያቀርባል።

በስራ እና የቴክኒካዊ ትምህርት (CTE) ጥላ ስር CCIC የምባለው ደግሞ ተማሪዎችን ለ 21 ኛው ክፍለ ዘመን የምያስፈልገዉን ለአካዳሚክ እና ለፕሮፈሽናል ብቁነት / ለማዘጋጀት የድስትሪክቱን የልማት ጥረት ያሰፋዋል። የተማሪዎች የመማሪያ ተሞክሮ አለ የተባለዉን ዘመናዊ የስራ አካባቢዎችን ይመስላል እንደዝሁም ትኩረቱም ተማሪዎችን በኢንዱስትሪ-ተኮር ባህል እና ድባብ ላይ ማስቀመጥ ነው።

የሁለተኛ ደረጃ ት / ቤቶች ሰፊ የCTE ፕሮግራሞችን መስጠትን ይቀጥላሉ። ይህ አዲሱ ማዕከል የአሁኑን ፕሮግራሞች ያሻሽላል በተጨማሪም የላቁና እና የተራቀቁ የትምህርት እድሎችን ለተማሪዎች ይሰጣል።

## በCCIC የምሰጡ ኮርሶች/ስልጠናዎች

1. ***አድቫንስድ ማኑፋክቸርንግ*** ፤ፋብሪኬሽን፤ድዛይን ፤ ሶሊድ ዎርክስ፤ ሜካቲሮኒክስ
2. ***የንግድ አገልግሎቶች*** ኢንተርፕሪነርሺፕ ፤ትብብር እና ግንኙነት,፤ ለደርሺፕ፤ የስራ ቦታ ሙያዊ ክህሎቶች።
3. ***የምግብ አዘገጃጀት/ሆቴሎች ምግብ፤*** የምግብ ማብሰል ሙያ፤ የሆቴሎች አመራር፤ ሥነምግብ፤ የምግብ አዘጋጋጃጀት ሙያ፤ ሆቴል/ርሶርት አስተዳዳር፤የተለያዩ ዝግጅቶን ማቀናበር
4. ***ጤናና የደህንነት ፋርማሲ*** ቴክኒሽያን ፤ የጤና ረዳት፤ፍዝካል ቴራፒ፤አክፐሽናል ቴራፒ ፤ የስነምግባር ሳይንስ ቴክንሽያን የስፖርተኖች ሃክም
5. ***የመሠረተ ልማት ምህንድስና*** የኮንስትራክሽን ማነጅመንት፤ የቧንቧ ሥራ፤ ኤሌክትሪካል፤ የሙቃትና የቅዝቃዜ መቆጣጣሪያ ስሥተም (HVAC, )የግድግዳ ስራ፤ የወለል ሥራ፤ የጣራ ሥራ
6. ***እንፎርሜሽን ተከኖሎጅ/(STEAM)*** የኮምፕዩተር ደህንነት፤ ኢንፎርሜሽን ተከኖሎጅ፤ የዲዛይን ቤተ-ሙከራ፤ ቪርቹል ሊአልትይ (ምናባዊ እውነታ) ሮቦቲክስ፤ሮቦቶች፤ ትልቅ ውሂብ (ዳታ)
7. ***ትራንስፖርተሽን*** (አውቶሞቲቭ፤አቪዬሽን የመኪና ቴክንሽያን፤ቀላል የድዝል ዘይት ፤የአውሮፕላን ሜካንክ፤ የበረራ ስልጠና ፤እና አውቶማቲክ ወይንም ፓይለት አልባ ቀላል /ትናንሽ አውሮፕላኖች( Drone) ቴክኖሎጅ

### ተማሪዎች ይህንን አቅርቦት/ኮርሶች እንዴት ልያገኙት ይችላሉ?

ተማሪዎች ከአማካሪዎቻቸው እና ከCTE መምህራን ጋር በመተባበር በማመልከቻ ሂደት በ CCIC በኩል ኮርሶችን ያገኛሉ።

### ይህ አማራጭ አሁን ካለው የሥራ አዝማሚያ ጋር እንዴት ይዘመዳል?

በ CCIC የሚሰጡት ሁሉም ኮርሶች በኮሎራዶ የአስተዳደር ልማት እና ዓለም አቀፍ ንግድ ቢሮ እና በኮሎራዶ ኮምዩኒቲ ኮሌጅ ሲስተም በተደረገው ጥናት ውስጥ እንደተገለፀው ለኮሌጅ እና ለሥራ እድሎች እንደ መጀመሪያው መንገድ ያገለግላሉ።ሁሉም በCCIC የምሰጡት ኮርሶች /መንገዶች እጅግ በጣም ተፈላጊ ወደሆኑት የስራ መስኮች ይመራሉ።

### ይህ እንዴትና/ በምን መልኩ በምረቃ መስፈርቶች ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል?

CCIC የምባለው ማዕከል ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ እንድያገኙ የምረዳቸው አንድ ተጨማሪ ሃሴት ነው። ተማሪዎች በዝህ መስመር/ፕሮግራም በእያንዳንዱ ትምህርቶች ፤ በሂሳብ በሳይንስ እና በእንግሊዝኛ እንደዝሁም አማራጮችንም ጨምሮ ነጥቦችን /ክሬድቶችን ልያገኙ ይችላሉ። እንደዚሁም በመረጡት መስክ ላይ በመመርኮዝ፤ ተማሪዎች በCCIC ክፍሎች ውስጥ ሲሳተፉ የኢንዱስትሪ ማረጋገጫዎችን እና በተመሳሳይ ጊዜ የኮንከረንት እንሮልመንት ነጥብ/ክረዲት ማግኘት ይችላሉ።

### ለበለጠ መረጃ

CHERRY CREEK
INNOVATION CAMPUS

**ማርክ ሞርጋን(Mark Morgan,) የትምህርት ቤቱ ረእሰ መምህራን**

720.554.4561 ቢሮ

እሜይል
dmorgan18@cherrycreekschools.org

**ጄይ ሙር(Jay Moore) የCTE አስተባባሪ**
720.554.4995 ቢሮ

እሜይል
jmoore@cherrycreekschools.org

**ስንድይ ጆንሰን(Cindy Johnson) ዋና ጸሃፊ**
720.554.4559 ቢሮ
cjohnson160@cherrycreekschools.org



# እቅድ ማውጣት እና

መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ለመዘጋጀት ወሳኝ ጊዜ/ወቅት ነው።ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ በምን የሙያ መስክ እንደምሰማሩ ባያውቁም በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያዳብሯቸው አካዴሚያዊ እድገቶች ፤ ማህበራዊ ችሎታዎች፤ የስራ ልምዶች እና ፕሮብሌም አፈታት ችሎታዎች ለወደፊቱ ስኬታቸው በማዘጋጀት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

## ዕቅድ ማውጣት

በNaviance ድረገጽ ዉስጥ የምገኘው (ICAP)የምበለው ይህም በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የግል የሙያና የአካዳሚክ ዕቅድ ማዉጫ የሆነዉ ለሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ዝግጁነት፤ዕቅድ ለማዉጣትና ለስኬታማነት ለመዘጋጀት የምረዳ አንዱ መንገድ ነው። S.M.A.R.T የምባሉት ግቦች ከሁለተኛ ደረጃ ግብዎ ጋር መጣጣም አላባቸው እንደዝሁም የእራስዎን ግስጋሴ/ስኬት ለመቆጣጠር ጥሩ መንገድ ናቸው። ለስራዎች መጋለጥህ/ሽ ችሎታህን/ሽና ፍላጎትህን/ሽን የበለጠ ለማወቅና እነዝህን ችሎታዎችና ፍላጎቶችህን/ሽን ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችህ/ሽ አመረረጥ ጋር እንዲታጣጥም/ሚ ይረዳሃል/ሻል ። ፍላጎቶችህን/ሽን እና የአካዳሚክ ችሎታዎችህን/ሽን ማወቅ በሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ተገቢውን የኮርሶች ደረጃ እንዲትመርጥ/ጭ ይረዳሻል/ሃል።

## ስኬታማ የመከከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ

በመሠረታዊ ደረጃ፤ የመካከለኛ ደረጃ ት / ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ የመማር ልምዶችን፤ ለምሳሌ የማቀናበር ክህለቶች፤ከመምህራኖቻቸው ጋር የመግባባት ችሎታን ማሳየት አለባቸው እንደዝሁም የተለመደ የቤት ሥራ የመስሪያ ጊዜም ልኖረቸው ይገባል። የመካከለኛ ደረጃ ት / ቤት ተማሪዎች፤ በወላጆች፤በመምህራን እና በትምህርት አማካሪዎች ድጋፍ ከዝህ በታች ያሉትን ማድረግ ይችላሉ።

- የግል ፍላጎቶቻቻዉን ችሎቶቻቸዉን እና ጥንካሬዎችን ይለያሉ
- ቤት፤ስራ እና / ወይም ትምህርት ቤት በማህበረሰቡ ውስጥ ከለው ከስራ ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ መግለጽ
- ለሁሉም ሰዎች ስራ እንዴት አስፈላጊ እነደሆነነ እንደዝሁም ሁሉም ሰው በሥራ ላይ ልሰመራ እንደምችል ያብራራሉ
- የግል እምነት እና እሴት እንዴት በውሳኔ አደረረግ ላይ ተጽህኖ እንደምያደርጉ ይገልጻሉ።
- ከሌሎች ጋር ለመስራት ውጤታማ ክህሎቶችን ያሳያሉ
- በሰዎች መካከል ላሉት መመሳሰልና እና ልዩነቶች አድናቆትን ያሳያሉ
- ግጭታን/ሃላፍነትን ለመፈፀምየሚያስፈልጉየግለሰብክህሎቶችንእና ችሎታዎችንያብራራሉ.
- በተለያዩ ሙያዎች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ክህሎቶችን ያብራራሉ
- ሥራ ለማግኘት እና ለመቀጠል የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ማሳየት.

በመለስተኛ ደረጃ ት / ቤት ለኮሌጅ እና ለስራ ለመዘጋጀት ተጨማሪ ዕድሎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

## የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአካዳሚክ ፕሮግረም

መካከለኛ ደረጃ ት / ቤቶች በኤለመንተርይ መሰረታዊ ትምህርቶች ላይ ይገነባሉ እንደዝሁም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ጠንካራ መሰረትንም ያረጋግጣሉ።. ከመሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሙ በተጨማሪ እያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ት / ቤት ማመልከቻ ሊፈልግ የሚችል ልዩ ፕሮግራም ሊያቀርብ ይችላል.



# የመከከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት  አስፈላጊነት

## ለመካከለኛ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ  የመርሃ ግብሮች ፕሮግራም ( ፖሊሲ IHA):

"የመሃከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በይዘት ደረጃዎች  መመሪያዎች መሰረት  ግምገማዎችን እነ ትምህርቶችን መስጠታቸውን ይቀጥላሉ።ይህ የትምህርት አይነቶች የቋንቋ ስነጥበብ፤ ሂሳብ፤የሳይንስና ማህበራዊ ትምህርቶች፤ የሲቪክ፤የጂኦግራፊ፤ የታሪክ እና የኢኮኖሚክስ ትምህርቶችን ጭምር ያካትታል። በተጨማሪም  ተማሪዎች የይዘት ደረጃዎች መመርያ መስፈርትን በምያሟሉና   እንደ  አማራጭ በምሰጡት  የትምህርት አይነቶች በኩል ያላቸውን ችሎታ እና ፍላጎታቸውን ለማስፋት እድሉ ይኖራቸዋል።

በእያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ት / ቤት በተወሰነ  መሰረት ይህ የአማራጭ ትምህርት ፕሮግራም  ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ኮርሶች ያካተተ ሊሆን ይችላል-የኪነጥበብ/ስዕል፤ሙዚቃ፤ቴክኒካል ትምህርት፤ የተለያዩ  ቋንቋዎች፤ የሰዉነት ማጎልማሻ/ስፖርት፤ ጤና፤እና የቤተሰብ ጥናቶች፤ኮምፒተር / ክቦርድ / ንግድ እና ሌሎች አግባብ ያላቸው የመካከለኛ  ኮርሶችን ይሆናል።የመካከለኛ ደረጃ  ት / ቤቶች ተማሪዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማዘጋጀት ተጨማሪ ዕገዛዎችን ያቀርባሉ። እንደዝሁም  ተማሪዎችን ሰለ ስና ምግባርና ደንብ ያስተምራሉ እንደዝሁም ተማሪዎች የሥነ-ምግባር  ደንቡንም  እንዲከተሉ ይፈልጋሉ።. በተጨማሪም  የስምንተኛ-ክፍል ተማሪዎች ለዘጠነኛ ክፍል  ኮርሶቻቸው ከመመዝገባቸው በፍት  የትምህርት ቤቱ  ድስትርክቱ  የኮሎራዶ  የከፍተኛ ትምህርት  መግቢያን  መመርያዎችን  የምያሟሉና ያለቸዉን የኮርሶች ዝርዝር  ይፋ ያደርጋል  እንደዝሁም   ለተማሪዎችና  ወይም ወላጆች / አሳዳጊዎች ይሰጣል።

## በለልዩ ተሰጥዎና  ችሎታዎች  ተማሪዎች

ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ  እንዳላው/ላት የታወቀ ማንኛዉም ተማሪ የክፍላቸዉን ካርኩለም የምደግፍ  ችሎታቸዉና ፍላጎታቸዉን የምያሟላ የተለያየ ፕሮግራም ይኖራቸዋል። የቡድን አቀራረብን በመጠቀም፤ ፕሮግራሙ ለፍላጎቶች ምላሽ ይሰጣል፤ብዙ ተሰጥኦዎችን ፤ ተሞክሮዎችንና  እና ልዩነትን ያገናዝባል. የዲስትሪክቶቹ  በምርምር ላይ የተመረኮዘ ስትራቴጂዎች ከአካዳሚክ ችሎታዎች ጋር የተጣጣሙ ምርጥ የትምህርት እድሎችን ያቀርባሉ።

## የመካከለኛ ደረጃ  ትምህርት ቤት የዓለም/የተለያዩ ቋንቋዎች

በመከከለኛ ደረጃ ት/ቤት ዉስጥ የምስጡት የዓለም ቋንቋዎች ትምህርት  በመጪው ዓመታት ውስጥ ለቀጣይ አመታት ለረጅም ጊዜ ስኬታማነት ወሳኝ ነው።ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች የሌሎቹን በህሎች በምያከብሩ  በተለያዩ ባህሎች/ቋንቋዎች ዉስጥ እንድሳተፉና ለአለም ዝግጁ እንድሆኑና እንድግባቡ ለማዘጋጀት ነው። በመለስተኛ ደረጃ ት / ቤት የዓለም/የተለያዩ  ቋንቋን የሚያጠኑ ተማሪዎች የላቀ የንግግር ችሎታና  እና ተነሳሽነት አላቸው። የዓለም ቋንቋ እንደ  አማራጭ የምስጥና የሚበረታታ ሲሆን ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ሊለያይ ይችላል።



# የማቀጃ መሳሪያዎች

## የግል የሙያ እና የአካዳሚክ እቅድ (ICAP)

በቼሪ ክሪክ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለምረቃ እና ከዚያም በሻጋር እቅዶቻቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። ICAP ገና ከ6ኛ ክፍል የምጀምር ህደት ስሆን ከሁለተኛ ደረጃ ምርቃት በሃላ ያለው እቅድህ/ሽ ከመርጥከው/ሽው መንገድ ጋር እንደምጣጣም ለማረጋጋጥ ለግል የኮርስ ዕቅድ ወሰኝ መሰረትን ይጥላል። የICAP ዕቅድህ/ሽ ከመካከለኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድረስ እነ እስከ 12 ኛ ክፍል ድረስ ይከተልሃል/ሻል። የICAPS ዕቅዶች እነዝህን ያጠቃልላሉ።

- የሥራ ዝግጅት ጥናት፤የፍላጎትየዳሰሳ ጥናቶችን ጨምሮ
- አካዴሚያዊ ሂደቶች እነዝም፦የተወሰዱ ኮርሶች የምምገማወጤቶችያጠቃልላል።(PSAT,SAT,ACT Aspire, Pre-ACT);
- በአዉድና በአገልግሎት ትምህርት የተገኙ ተሞክሮዎች;
- የኮሌጅ ማመልከቻዎች እና የስራ ልምዶች ልክ ዝግጁ ሆነው ገቢ እንደሆኑበት ሁኔታ

በተማሪው/ዋ የትምህርት ክንዉን መሰረት የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች ለምሳሌ በኮንከረት እንሮልመንት ኮርሶች ተማሪው/ዋ ያስመዘገበችው/በው ዉጤቶች

## Naviance የምባል የተማሪዎች ድረገጽ

Naviance ለሁሉም ተማሪዎች እና ወላጆች ለኮሌጅ እና ለሥራ እቅድ ዝግጅት ክፍት የሆነ አጠቃላይ ድረገጽ ነው። Naviance Student የምባለው የያንዳንዱ ተማሪዎች የግል የሙያ እና የአካዴሚያዊ ዕቅድ (ICAP) የምፈጠርበትና የሚቀመጥበት እና እንደዝሁም የምቆጣጣርበት ድረገጽ ነው። የNaviance Student ድረ ገጽን ለማግኘት ወደ ድስትርክታችን ዋና ድረ-ገጽ በመሄድ Naviance Student የምለዉን ልንክ ይጫኑ። ስለ Student Naviance ወይም ICAP በተመለከተ ጥያቄዎች ከለዎት እባክዎ ሊያግዝዎት የምችሉትን የት / ቤትዎ አማካሪን ያማክሯት/ሩት።


በተጨማሪ Naviance Student የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ያስችልዎታል:

- ለወደፊቱ እቅድ ማውጣት - የአራት-ዓመት እቅድ፤ የመማር ዘይቤን መቀየስ፤ የሥራ ልምድን ማመልከቻን ማዘጋጀት ፤ እና የሥራና የፍላጎቶች ዝርዝር ማዉጣት ፤ለኮሌጅና ለሥራ ዕቅዳቸው ይበልጥ ለማዘጋጀት Naviance Student በምባለው ድረ-ገጽ ዉስጥ ICAP በምባለው የ ዕቅድ ማዉጫችው ዉስጥ የተመደበዉን ሥራ ተጠናቅቃላችው።
- መግባት ስለምትፈልጉት ኮሌጆች አጥኑ - የመግቢያ መስፈርቶችን፤ለምሳሌ እንደ ጠቅላላ ዉጤት(GPA) እና መደበኛ የተማሪዎች የፈተና ውጤቶች እንደዝሁም የተማሪዎች የአትሌትክስ ፕሮግራሞች እና ሌሎች ብዙ ነገሮችን ያወዳድሩ.
- ስለ የሰመር የማጠነካርያ/ ትምህርት እድሎች አጥኑ

ሰለ ICAP እና Navian Student ተጨማሪ መረጃ በዝህ ድረገጽ ሊገኝ ይችላል
**www.cherrycreekschools.org/InclusiveExcellence/Pages/default.aspx**



# ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት መሸጋገር




ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሸጋገር ሁለት የተዘበረረቀ ስሜት ልያመጣ ይችላል ያለመረጋጋት ስሜትና እና ብሩህ ተስፋ ፤ አዳዲስ የክፍል ጓደኞች፤ አዳዲስ መምህራን እና አዳዲስ ደንቦች፤ እንዲሁም ብዙ እድሎችም ይኖሯችዋል። የመለመማድ/የልምጃ ጊዜ መኖሩ የተለመደ ነው። ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልምምድ/ልምጃ ጥቂት ጠቃሚ ምክሮች እነሆ-

**1.ሎጅስቲኩን ይማሩ..** ዝግጁ ሁን/ኚ ሎከርህ/ሽ የት እንደሆነና አከፋፋቱንም እወቅ/ቂ፤ የህንፃው/የክፍሎቹን አቀማመጥ እወቅ/ቂ ፤ የመማርያ ክፍል መርሃ ግብርህን/ሽን ( ስኬጁል) እና አንዳንድ ጠቃሚ ቁሳቁሶችንም እወቅ/ቂ። የትምህርት ቤቱ የአማካሪዎች ቢሮ የት እንደሚገኝ እና ማንኛውም የምሰጡ የማጠናከርያ ትምህርት እድሎች ምን እንደሆኑ እወቂ/ቅ። የደወል ጊዜውን እና ከአንዱ ክፍል ወደሌላ የመተላላፍያ ጊዜውን እወቅ/ቂ..

**2. ችግሮችን መፍታት እወቅ/ቂ** እንደ ተማሪ መብትህን/ሽን ከአንተ/አንች በላይ የምያስጠብቅ የለም እንደዝሁም ችግርን የመፍታት ችሎታ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለህ/ሽ የምትመረው/ማሪው የምትለመመደው/ጅው ትልቅ ችሎታ ነው። ከሁሉም በተሻለ መልኩ እንደ ተማሪ ፍላጎቶቻችው ምን እንደሆኑ ተውቃላቸው ፤ እንደዝሁም የችግርን አይነቶችን ለይተው ማወቅ እና የተሻለውን ድጋፍ ለማግኘት በአካባቢያችሁ ያሉትን ረሶርሶችንም/ድጋፎች ማግኘት ይችላሉ።ያሉት ድጋፎች መምህራን ፣ አማካሪዎች ወይንም በትምህርት ቤቱ ዉስጥ የምገኙ ቤተመጻሃፍት ወይም አካዴሚያዊ ግብዓቶች/ድጋፎች ሊሆኑ ይችላሉ።

**3. የትምህርት/ግስጋሴህን/ሽን ተቆጣጣር/ሪ** በትምህርትህ/ሽ/ በኩል ምን ደረጃ ላይ እንዳለህ/ሽ እንደዝሁም ቅድሚያ የምሰጠዉን ነገር ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። መምህሮችዎ ስለ ትምህርትዎ ጉዳይ ከቤተሰብዎ ጋር ይነጋጋራሉ ብለው አይገምቱ ።ስለ ትምህርታችው ጉዳይና ግስጋሴ/መሻሻል ኃለፍነት ዉሰዱ እንደዝሁም የቤት ስራዎቻችሁን፤ ዉጤታችሁንና እንደዝሁም አቴንዳንሳችሁን ለመቆጣጣር PowerSchool የምባለዉን ድረገጽ ይጠቀሙ።

**4. መደበኛ የሆነ የስራ መርሃ ግብር አዉጣ/ጪ.** የሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ተማሪ እንደመሆንህ/ሽ መጠን ስራ በጣም ይባዛባችኋል እና የጊዜ አጠቃቃምን መቆጣጣር መማር ቁልፍ ነው። አንዳንድ ተማሪዎች እንድያመቻቸው የዕቅድ ማዉጫ ደብተር ( ፕላነር)ይጠቀማሉ። መደበኛ ፕሮግራምን ማመቻቸት የአካዳሚ ትምህርቶችን፤ አትሌቲክስንና የማህበራዊ ኑሮን ሚዛን ለመጠበቅ ይረዳሃል/ሻል።

**5. በክለብ ወይም በስፖርት ዉስጥ ተሳተፍ/ፊ** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት "የልብ ምት"( ነፍስ መዝራት) የምጀምረው በክለቦች እና በስፖርት ዉስጥ መሰተፍ ስትጀምር/ሪ ነው።ጥናቶች እንደሚያሳዩት ተማሪዎች ከት / ቤት ጋር መላመድ/መያያዝ ስጀምሩ የትምህርት ክንውናቸዉም ይሻሻላል። የአትሌትክስንና የስፖርት እንቅስቃሴን ዕድሎችን ዝርዝር ለማወቅ የትምህርት ቤትዎን የአትሌትክስንና እንቅስቃሴዎችን ቢሮዎችን ይጎብኙ

**6. ግንኙነትን ያዳብሩ/ይገንቡ** አማካሪህን/ሽን እና መምህራኖችህ/ሽ ጋር መተወወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። አማካሪዎችህ/ሽ እና አስተማሪዎችህ/ሽ ለአንተ/አንቺ በጣም ጥሩ የሆኑ ተቆርቋሪ/ አሳቢ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም ስኬታማነታችውን ለማረጋገጥ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር አብሮ ለመሥራት ይፈልጋሉ.

**7.ጥያቄዎችን ጠይቁ** ነገሮች ትክክል ሳይሆኑ ስቀሩና ወይንም ስጋት ካለዎት ጥያቄዎችን ጠይቁ.



# የምረቃ መስፈርቶች

## የነጥብ /ዉጤት መስፈርቶች

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ተማሪዎቹን ለኮሌጅ እና ለስራ ስኬታማነት ለማዘጋጀት ጠንካራ/ጥብቅ የሆኑትን የአካዳሚ ትምህርት መርሃ ግብር መስጠቱን ይቀጥላል። የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልምድዎ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመዘጋጀቱም በላይ ዕቅድ ለማዉጣትና ለሥራ ፍለጋም አገልጦችዋል። ሁለተኛ ደረጃ ት / ቤቶች የተማሪዎችን የግል ፍላጎት በሁሉም ስነትምህርት በኩል የምያሟሉ በጣም ብዙ አስደናቂ ነገር ግን ጥብቅ የሆኑ በርካታ የተላያዩ ኮርሶችን ያቀርባሉ። በ2019 የምከፈተው ዘመናዊ የቼሪ ክሪክ ኢኖቬሽን ካምፓስ እያደገ የሚሄደውን ዓለም አቀፋዊ ማህበረሰብ ፍላጎት ለማሟላት ተጨማሪ መንገዶችን ያቀርባል.

ለምረቃ በትክክለኛው መንገድ ላይ መሆንህን/ሽን ለማወቅ የምያስፋልጉትን የነጥብ መስፈርቶች ሂደትን መከታተል ትችላለህ/ሽ. በትምህርት አመቱ መጨረሻ፤ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ቢያንስ ከ 6 እስከ 7 ክሬዲቶችንና የ10ኛ ክፍል ተማሪ ደግሞ 11 ክሬዲቶች እና የ11ኛ ክፍል ተማር ደግሞ 17 ክረድቶችን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለበት/ባት። አማካሪዎቻችው ኮርሶቻችዉን ማጠናቀቃችዉን፤እነ ለመመረቅ የምያስፋልጋችዉን ክረድትን በተመለከተ ዕቅድ በማዉጣትና እና በመከታተል ሊረዷቸው ይችላሉ። ወደ Powerschool ድረገጽም በመሄድ ሁሉንም ዉጤትህን/ሽን/ክረድትህን/ሽን ማየት ትችላለህ/ያለሽ.

ከማንኛውም የቼሪ ክሪክ ት/ቤቶች ድስትርክት የሚመረቁት ሁሉም ተማሪዎች ለምረቃ የምያስፋልገዉን ቢያንስ 22 ነጥቦች ማሟላት አለባቸው።

## በእንግሊዝኛ እና በሂሳብ ትምህርትቶች መተያት ያለበት ብቃት

በ2021 እና ከዚያ ቦሃላ የሚመረቁ ተማሪዎች ለመመረቅ ከሚያስፈልጉት 22 ክሬዲት በተጨማሪ በእንግሊዝኛ እና በሂሳብ ብቃታቸዉን ለኮሌጅ እና ለስራ መስክ ዝግጁነታቸዉን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።
የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክቱ እነዚህን ችሎታዎች ሊያሟሉ የሚችሉባቸውን የተለያዩ መንገዶች ይፋ አድርጓል። (IKF-E).



## የምረቃ መስፈርቶች ለ 2019 እና ለ 2020 ተመራቂዎች

**(በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ IKF እንደተገለጸው)**

| የትምህርት ዓይነት | የሚያስፈልጉ ነጥቦች |
|---|---|
| የእንግልዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ...................... | 4 |
| ማህባረሰዊ ጥነት(ሶሻል ስተድስ) * ...................... ...... | 3 |
| ሕሳብ ........................... | 3 |
| ሳይንስ .............................. | 3 |
| የዓለም ቋንቋዎች......................... | 0 |
| ፋይን/ፕራክትካል አርትስ ......... | 1.5 |
| ስፖርት/ጤና ......... | 2 |
| አማራጮች (Electives)......... | 5.5 |
| አጠቃላይ ......... | 22 |

**ለ2ተኛ ደረጃ ምረቃ የምያስፋልጉ 22 ነጥቦች**

ኮርሶችዎን ሲመርጡ, ከምረቃ መስፈርቶች በላይ መመልከትዎን ያረጋግጡ እና ወደ ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች ለመግባት የሚያስፈልጉትን አነስተኛ መስፈርቶችንም ያረጋግጡ.

** ለማህበራዊ ጥናቶች ከሚያስፈልጉት (3) ክሬዲቶች ዉስጥ 1.0 ክሬድቱ የአሜርካን ታሪክ ለአንድ ሙሉ ዓመት መወሰድ አለባት .5 ደግሞ ለግማሽ ሴምስተር የሲቭክስንና / መንግስት ትምህርት መሆን አለባት ።*

# የምረቃ መስፈርቶች ለ2021ና ከዝያ ቦሃላ ላሉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ተመራቂዎች

**(በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ IKF ዉስጥ እንደተገለጸው)**

| የትምህርት ዓይነት | የሚያስፈልጉ ነጥቦች |
|---|---|
| የእንግልዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ | 4 |
| ማህባረሰዊ ጥነት(ሶሻል ስተድስ) | 3 |
| ሕሳብ | 3 |
| ሳይንስ | 3 |
| የዓለም ቋንቋ | 0 |
| ፋይን/ፕራክትካል አርትስ | 1.5 |
| ስፖርት/ጤና | 2 |
| አማራጮች(Electives) | 5.5 |
| አጠቃላይ | 22 |

**ለማህበራዊ ጥናቶች ከሚያስፈልጉት (3) ክሬዲቶች ዉስጥ 1.0 ክሬድቱ የአሜርካን ታሪክ ለአንድ ሙሉ አመት መወሰድ አለባት .5 ደግሞ ለግማሽ ሴምስተር የሲቭክስንና / መንግስት ትምህርት መሆን አለባት*



## ለኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት በንባብና በሂሳብ ትምህርቶች መተየት ያለባቸው ብቃቶች

### ለ2021 እና ከዛ በኋላ ላሉ ተመራቂዎች

**(በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ IKF ዉስጥ እንደተገለጸው)**

ከ2021ተመራቂዎች ጀምሮ እያንዳንዱ ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቃቅያ ድፕሎማ ለመቀበል ለምረቃ ከምያስፈልጉት 22 ነጥቦች በተጨማሪ በንባብና በኀሳብ ትምህርት ለኮሌጅና ለሥራ/ዝግጁነት ብቃት ሊያንፀባርቅ ይገባል ። የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ተማሪዎች ትምህርታቸውን እና ዝግጅታቸውን ለማሳየት እንድችሉ የተለያዩ ብዙ አማራጮችን ያቀርባል።

ተማሪዎች እነዚህን አማራጮች ከቤተሰቦቻቸው፤ከአማካሪዎቻቸው እና ከመምህራኖቻቸው ጋር እንድወያዩና እንዲከታተሉ ይበረታታሉ.

# ለመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች የተማሪ እቅድ አወጣጥ

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የICAP/የስራ:ዕቅዶች/መንገዶች | | | | | ፍላጎትና ክህሎቶች- | | | |
| የሁለተኛ ደረጃ የምረቃ ዕቅድ | | | | | | | | |
| | እንግልዝኛ | ሒሳብ | ሳይንስ | ሶሻል ስተድስ | አማራጮች/ እለክትቭስ | | | |
| 6 | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | |
| ከ ICAP ዕቅዶቹ ጋር የተጣጣሙ አግባብነት ያላቸው ልምዶች | | | | | | | | |
| 1 | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | |

ማስታዋሻ ____________________________________________

# ለ 2019 እና ለ 2020 ተመራቂዎች የዕቅድ አወጣጥ

| የICAP/የሥራ ዕቅዶች/መንገዶች | ኮሌጅ፤<br>ድግሪ/ፕሮግራም |
|---|---|

| የሁለተኛ ደረጃ የምረቃ ዕቅድ | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እንግልዝኛ | ሒሳብ | ሳይንስ | ሶሻል ስተድስ | ስነጥበብ/ሰእል | ጤና | ስፖርት | አማራጮች |
| 9 | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | |
| 11 | | | | | | | | |
| 12 | | | | | | | | |
| ተማሪዎች በ2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትእያሉ የወሰዱት የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ወይንም የኮንከረንት እንሮልመንት ኮርሶች | | | | | | | | |
| 13 | | | | | | | | |
| 14 | | | | | | | | |
| 15 | | | | | | | | |
| 16 | | | | | | | | |

ማስታወሻ

## ለ2021 እነ ከዝያም ቦሃላ ተመራቂ ተማሪዎች የእቀድ አወጣጥ

| የICAP/የሥራ ዕቅዶች/መንገዶች: | ኮሌጅ፤<br>ድግሪ/ፕሮግራም |
|---|---|

| የሁለተኛ ደረጃ የምረቃ ዕቅድ | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እንግልዝኛ | ሒሳብ | ሳይንስ | ሶሻል ስተድስ | ስነጥበብ/ሰእል | ጤና | ስፖርት | አማራጮች |
| 9 | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | |
| 11 | | | | | | | | |
| 12 | | | | | | | | |
| ተማሪዎች በ2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ የወሰዱት የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ወይንም የኮንከረንት እንሮልመንት ኮርሶች | | | | | | | | |
| 13 | | | | | | | | |
| 14 | | | | | | | | |
| 15 | | | | | | | | |
| 16 | | | | | | | | |

## የእንግሊዘኛ / የቋንቋ ስነ-ጥበብ እና የሂሳብ ብቃት ችሎታ መቆጣጣርያ ስትጭርስ/ሽ በዝርዝሩ ላይ ጻፍ/ፊ

እንግልዝኛ____________________

ኅሳብ ____________________

# በእንግልዝኛና በአንድ ወይንም ከዝያም በላይ ሌሎች ቋንቋዎች ችሎታ ብቃት ማረጋጋጫ
# Seal of Biliteracy

ሲል ኦፍ ባይሊትረስ የምባለው ( **Seal of Biliteracy**) በእንግልዝኛና በአንድ ወይንም ከዝያም በላይ የቋንቋ ችሎታ ማረጋጋጫ ሽልማት /ሰርትፍኬት በኮላራዶ የትምህርት ድፓርተመንት ወይንም በትምህርት ቤቶች ድስትርክት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቃያ አመት ላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርትና በአንድ ወይንም ከዝያም በላይ በአለም ቋንቋዎች ላይ ብቃታቸዉን ላሳዩት ለ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች የምሰጥ ነው።ይህ የቋንቋ ችሎታ ዕዉቅና የሁለተኛ ደረጃ ቋሚ ትራንስክርፕት ሆኖ ይቆያል። ይህ የችሎታ ማረጋጋጫ ማህተም ለተማሪዎች ከእንግልዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአንድ ወይንም ከዝያም በላይ ቋንቋዎች ችሎታቸዉን/ብቃታቸዉን ለማረጋጋጥ ያገለግላል እንደዝሁም የተማሪዎችን ለኮለጅና ለስራ ዝግጁነት እንደሁም በአለማቀፍ ማህበረሰብ ዉስጥም የመሰተፍ ብቃታቸዉን የምገልጽ መግለጫ ነው

### ሲል ኦፍ ባይሊትረስ ( Seal of Biliteracy) አስፋላጊ የሆነበት ምክንያት

- ቋንቋ እንደ ሃብትና መብት መሆኑን ያሳያል
- ቋንቋን እንደ እሴቶች በመቁጠር ዋጋ መስጠት
- ተማሪዎቻችንን ለኮሌጅ እና ለስራ ማዘጋጀት
- የቋንቋ ልዩነት እና ማንነት ዋጋ እንዳለው ያስገነዝባል
- ለቋንቋ ችሎታና ብቃት ዕውቅናን ና ግንዛቤን ይሰጣል።
- ተማሪዎችን በ21ኛው ክፍለ ዘመን 'በሥራ ገበያው እና በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ውስጥ በሚጠቅሟቸው ክህሎቶች ማዘጋጀት
- ለዩኒቨርሲቲዎች፤ ቀጣሪዎችና ፤ስኮላርሽፖችና ብድር ሰጪዎች 2 ወይም ከዚያ በላይ የቋንቋዎች ብቃትና ከፍተኛ አካዳሚክ ችሎታና ትጋት ያለቸዉን ዕጩ ተማሪዎችን የማወቅ ዘዴን ይሰጣቸዋል።
- በቡድን መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ያጠናክራል እንዲሁም በማኅበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ባህሎችን እና ቋንቋዎችን ያስከብራል

በቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ውስጥ ተማሪዎች ይህንን የቋንቋ ችሎታ ብቁነት ማረጋጋጨ (Seal of Biliteracy) ለማግኘት ሁሉንም የምረቃ መስፈርቶችን ማሟላት ፤ በእንግሊዝኛ ቋንቋና እና ቢያንስ በአንዱ የዓለም ቋንቋ የማንበብና መጻፍ ችሎታ ልኖራቸው ይገባል።

ሰለ **CCSD Biliteracy** የበለጠ ለማወቅ ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ። http://cherrycreekschools.org/InclusiveExcellence/Pages/Seal-of-Biliteracy.aspx .

# ሁሉንም ተማሪዎች ማዘጋጀት

ከሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ሲትመረቅ/ቂ ብዙ አማራጮች አለህ/ሽ። በቤተሰብህ/ሽ፤ በአማካሪህ/ሽ እና በአስተማሪዎችህ/ች ድጋፍ አማካይነት ፍላጎቶችህን/ሽን እና ግቦችህን/ሽን ለማሟላት እቅድ ማውጣት ትችላለህ/ሽ። ምርጫህ/ሽ ምንም አይነት አማራጭ ቢሆንም እንኳ እቅድህን/ሽን ቀደም ብለህ/ሽ ነው መጀመር ያለብህ/ሽ፡ ከዚህ በታች የምገኙት በግምት ዉስጥ ልታስገባ/ቢ የምትችለው/ይው የተወሰኑ የድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አማራጮች ነቸው።

| | |
|---|---|
| **የሥራ ላይ ልምምድ** | የሙያ ስልጠና/ልምምድ ፕሮግራሞች ለ11ኛና 12ተኛ ክፍል ተማሪዎች በጣም ጥሩ አማራጭ ናቸው። የሙያ ስልጠና/ልምምድ ገነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለህ/ሽ የእውነተኛን ዓለም ዓቀፍ ልምዶችን ፤እና ቀጣይነት ያለው ትምህርት/ልምምድ እነ ምክርን እንደዝሁም ልዩ ስልጠና እና አንዳንድ ጊዜም የስራ ዕድልን ከምሰጡ የኢንዱስትሪ አጋሮች ጋር ለመሥራት ይረዳሃል/ሻል። የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ድስትርክት ተማሪዎች የሙያ ስልጠና ከወሰዱባቸው ቦታዎች ምሳሌዎች:<br>• Micron<br>• CareerWise<br>• Oakwood Homes<br>• Intertech Plastics<br>• Reata |
| **ኮሚንቲ ኮሊጅ /አነስተኛ ኮሊጅ** | የኮሎራዶ እስቴት ከፍተኛ የኮሚኒቲ ኮሌጆችና አነስተኛ ኮሌጆች ዝርዝር አሉት። ለአራት አመት ስልጠናን ወደምሰጡት ኮሌጆች ዝውውር ዝግጅት ለማድረግ ለሁለት አመት ስልጠናን ከምሰጡ ኮለጆች ድፕሎማን፤ የኢንዱስትሪ የምስክር ወረቀት ወይም የጠቅላላ ዕውቀት ትምህርቶችን ( መሰረታዊ ትምህርቶች)መውሰድ ይችላሉ። |
| **የዝግጅት ዓመት ፕሮግራም** | የዝግጅት አመት የምባለው ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምረቃ ቦሃላና ለከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመመዝገብ መካከል ያለ አመት ነው ይህም ማለት ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ምርቃት ቦሃላ ቀጥታ ወደ ኮሌጆች ወይንም ዩኒቨርሲቲ ከመሄዳቸው በፍት ለአንድ አመት ያህል ያርፋሉ። ይህ የዝግጅት ዓመት ለወደፍቱ ትምህርታቸዉ ዕቅድ ለማዉጣት የምትዘገጁበት ጊዜ መሆን አለበት።. |
| **የዉትድርና አገልግሎት** | የአሜሪካ የአገር መከላከያ ፕሮግራም በዉትድርና አላም ለመሰማራት ለምፈልጉት በስሩ ብዙ ቅርንጫፎችና አማራጮች አሉት። ከተመረቅክ/ሽ በኋላ በፍላጎቶችህ/ሽ እና ክህሎቶችሽ/ህ ላይ ተመስርቶ ቀጥታ ወደ ውድትርና አገልግሎት ለመግባት ማመልከት ትችላላህ/ሽ ወይንም ወደ ወታደራዊ አካዳሚ/ስልጠና ለመግባት ማመልከት ትችላላህ/ችያለሽ። በወታደራዊ ስልጠና አካዳሚ ዉስጥ የአራት አመት ድግርህን/ሽን ተጠናቅቃለህ/ሽ ከዚያም ጎን ለጎን የመጀመርያዉን ድግርህን ማጠናቀቅ ተከትሎ ከፍተኛ የኦፍሴርነትንም/የፖሊስ ማዕረግ ለማግኘት መመዝገብ አለህ/ሽ/ህ። በወታደራዊ ሙያዎች ውስጥ ለመሳተፍ የምፈልጉ ተማሪዎች የሙያ Aptitude Battery (ASVAB) የምባል ፈተና ይወስዳሉ።ይህ ፈተና የተማሪዎችን የቃላት፤የአረፍተነገርና የህሳብ እንድሁም የመማዛዘን ችሎታቸዉን የምመዝን ነው። ወደ ወታዳራዊ ስልጠና አካዳሚ ትምህርት ቤት የመግባት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በተላይም መምረጥ የምፍልጉትን ኮርሶችና እና የማመልከቻ ሂደቱን በተመለከተ ከአማካሪዎቻቸው ጋር ማመከር አለባቸው. |
| **የሙያ ትምህርት ቤት** | የሙያ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ፈጣን ሥራን ማግኘት በሚችሉበት አንድ የተወሰነ ችሎታ ላይ እንዲያተኩሩ እድል ይሰጣቸዋል። እንደ የሙያ ትምህርት ፕሮግራም አካል፤ የሥራ ላይ ስልጠና ሊሰጥዎት ይችላል።የሙያ ትምህርት ፕሮግራሞች በሚሰጡት የጊዜ ርዝማኔና በስርቴፍኬት አይነቶቹ ይለያያሉ። የሙያ የምስክር ወረቀቶች ምሳሌዎች እነዝህ ነቸው<br>• ኮስሞቲሎጂ<br>• የመኪና ሜካኒክስ<br>• የእንስሳት ሐኪም ቴክንሽያን |
| **የአራት አመት ዩንቨርሲትይ/ኮሊጆች** | የኮሎራዶ ግዛት ለ4 አመት ስልጠናን የምሰጡ በግምት 20 የምሆኑ የሕዝብ እና የግል ኮሌጆች / ዩኒቨርሲቲዎችአሉት ከትናንሽ እስከ ትልቅ እና ከገጠር እስከ ከተማ እነዚህ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በምሰጡት የትምህርት አይነት ላይ ይለያያሉ በአራት-ዓመት ተቋማት ስርዓተ-ትምህርቱን የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች የባችለር ዲግሪ ያገኛሉ። ተማሪዎች የባችለር ዲግሪን ትምህርታቸዉን ተከትሎ ተጨማሪ የኮርስ / የፕሮግራም መስፈርቶችን በማሟላት የማስተርስ ወይም የዶክትሬት ደረጃ ትምህርታቸዉን ለመቀጠል መምረጥ ይችላሉ. |
| **በስራ አለም ላይ መሰማራት** | ለተማሪዎች ከ2ኛ ደረጃ ትም / ቤት ምረቃ ቦሃላ ቀጥታ ወደ ሥራ አለም መቀላቀል ሌላው አማራጭ ነው።እንደዝሁም እራሰቸዉን በገንዘብ የመርዳት ኃላፍነት ያለባቸው ልጆች የምፈልጉትን የስራ አይነት መርጠው በሥራ ላይ ልሰማሩ ይችላሉ። ለወደፊት የትምህርት ግቦቻቸው ገንዘብ ለማጠራቀም ለምፈልጉ ተማሪዎች ወደ ስራ አለም መሰማራት አንድ አማራጭ ነው። የሥራ ስምሪትን በተመለከተ ነጻ መረጃን ለማግኘት በአካባቢያቸው ከምገኙት የኮሎራዶ የሰው ሃይል አስተዳዳር ማእከላት አንዱን ይጎብኙ። |

# የኮሎራዶ የሕዝብ የአራት ዓመት ኮሌጅ እና ዩኒቨርስቲዎች የመግቢያ መስፈርቶች




በኮሎራዶ ያሉት  የአራት-ዓመት ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች አካዴሚያዊ ዝግጅቶች፤ በተለይ ደግሞ  በእንግሊዝኛ እና በሂሳብ ትምህርቶች, በቀጥታ ከስኬት ጋር የተዛመደ አመልካቾች መሆናቸውን ያውቃሉ። በኮሌጅ ዩኒቨርስቲ መግቢያ/ቅበላ ሂዳት ላይ በአካዳሚ ላይ ያተኮሩ ተማሪዎች  ተፈላጊ ነቸው እንደዝሁም  በበጎ አድራጎት ፤  አመራሮች፤  ርህራሄ የምያሳዩት ተማሪዎችም በቅበላው ሂዳት ላይ ምዛን ያነሳሉ።  የኮሌጅ መግቢያ መደበኛ  ፈተናዎች (ACT ወይም SAT) አማካኝ ውጤት መስፈርቶች  ከዩንቨርሲቲ ዩንቨርሲቲ  ሊለያይ ይችላል። ወቅታዊ የመግቢያ/የቅበላ  መስፈርቶችን በተመለከተ የያንዳንዱን  የኮሌጅ / ዩኒቨርሲቲ ማመልከቻ ጽ / ቤትን ወይም የትምህርት ቤትዎን ለዝህ ጉዳይ የተወከለዉን   አማካሪ ሁልጊዜ ይጠይቁ። ይህ ሠንጠረዥ እንደ መመሪያ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

**Colorado Higher Education Admission Requirements (HEAR)***

| | |
|---|---|
| English | 4.0 Credits |
| Social Studies | 3.0 Credits |
| Math | 4.0 Credits |
| Science | 3.0 Credits |
| Foreign Language | 1.0 Credits |
| Academic Electives | 2.0 Credits |
| **TOTAL** | **17.0 CREDITS** |

*Required for consideration to all four-year public colleges/universities in Colorado.

.

የከፍተኛ ትምህርት  ተቋማት የመግቢያ መስፈርቶች እንደ እስተቶችና ተቋማት ይለያያሉ።የመግቢያ መመዘኛዎችን በተመለከተ እያንዳንዱን ኮሌጅ / ዩኒቨርሲቲ በቀጥታ እንድያጣሩ  ይመከራሉ።

# የመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ግምገማዎች
# የቅድመ-ኮሌጅ ፈተናዎች

የACT ግምገማ ስርዓት ከአንደኛ ደረጃ እስከ የሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት ያካትታል እንደዝሁም ተከታታይ መገምገሚያዎችን በመጠቀም ስለኮሌጅ እና የስራ ችሎታዎችን በተመለከተ ለተማሪዎች፤ ለወላጆች እና ተማሪዎች ጥልቅ ማስተዋል ለመስጠት ታስቦ የተወቀረ ነው።

በየሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምሰጠው የACT ፈተና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ጠቅላላ የትምህርት እድገትን እና በእንግሊዝኛ፤በሂሳብ፤ በማንበብ እና በሳይንስ ዙሪያ ክህሎቶቻቸዉን በመገምገም የኮሌጅ ደረጃን ኮርሶች የማጠናቀቅ ችሎታቸውን ይገመግማል።

| የክፍል ደረጃ | ምዘና | የግድ የሚያስፈልግ ወይም የሚመከሩ | መቼ? |
|---|---|---|---|
| 6-9 | ACT Aspire | በድስትርክቱ ደረጃ የግድ የምያስፈልግ | ፎል |
| 10 | PreACT | በድስትርክቱ ደረጃ የግድ የምያስፈልግ | ፎል |
| 11 | ACT* | በድስትርክቱ የምመከር/የምቀርብ | ስፐሪንግ |

በ IKF-R የተቀመጠው የማለፊያ ውጤት ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁነት ተማሪዎችን በንባብ እና በሂሳብ ለመዘጋጀት የዲስትሪክቱን መስፈርቶችን ያሟላል።በተጨማሪም ተማሪዎች ለብሔራዊ የACT ፈተና ልመዘገቡና ፈተናዉን ለመዉሰድ መምረጥ ይችላሉ።
ስለ ብሄራዊ የACT ፈተናዎች ተጨማሪ መረጃ በ **www.act.org.** ላይ ይገኛል.

የ SAT የግምገማ ስርዓቱ የስቴቱ የግምገማ አካል ነው እንደዝሁም ሁሉም በኮላራዶ ግዛት ዉስጥ የምገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ልቀበሉት የምገባ ነው። SAT የምበለው ምዘና የኮሌጅ መግቢያ ፈተነ ስሆን የኮሌጆች የቅበላ ተወካዮች እንደ አንዱ የዉሳኔ አካል የሚጠቀሙበት የኮሌጅ መግቢያ ፈተና ነው. ፈተናው የንባብ፤ የፅሑፍ እና የሂሳብ መስኮች ላይ የተማሪዎችን ዕውቀት ይገመግማል።

| የክፍል ደረጃ | ምዘና | የግድ የሚያስፈልግ ወይም የሚመከሩ | መቼ? |
|---|---|---|---|
| 9 | PSAT | በድስትርክቱ ደረጃ የግድ የምያስፈልግ | ስፐሪንግ |
| 10 | PSAT | በድስትርክቱ ደረጃ የግድ የምያስፈልግ | ስፐሪንግ |
| 11 | PSAT/NMSQT | እንደ አማራጭ | ፎል |
| 11 | SAT* | በስቴቱ ደረጃ የግድ የምያስፋልግ | ስፐሪንግ |

በ IKF-R የተቀመጠው የማለፊያ ውጤት ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁነት ተማሪዎችን በንባብ እና በሂሳብ ለመዘጋጀት የዲስትሪክቱን መስፈርቶችን ያሟላል ።

በተጨማሪም ተማሪዎች ለብሔራዊ SAT ፈተና ልመዘገቡና ፈተናዉን ለመዉሰድ መምረጥ ይችላሉ። ስለ ብሄራዊ የ SAT ፈተናዎች ተጨማሪ መረጃ በ . **www.collegeboard.org.** ላይ ይገኛል.

# የኮሌጅ ዕቅድ ማውጫ ጊዜ

ለኮሌጅ መግቢያ ሂደት ቀደም ብሎ እቅድ ማውጣት ከአንተ/ች የምጠበቅ ኃላፍነት ነው። ከሁለተኛ ደረጃ ለመመረቅ በትክክለኛው መንገድ ላይ ስለመሆንህ/ሽና ወደመረጥከው/ሽው ኮሌጅ / ዩኒቨርሲቲ ለመግባትህ/ሽ እርግጠኛ ለመሆን በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ከት / ቤት አማካሪህ/ሽ ጋር ምክክር አድርጊ/ግ። የሚከተሉት በክፍል ደረጃዎች መሰረት የተቀናጁ የኮሌጅ እቅድ ማውጣት የጊዜ ሰሌዳ(timeline) ሰንጠረዥ ናቸው.

| 9ነኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|
| ከአማካሪህ/ሽ ጋር ተገናኝ/ኚ | የትምህርት መርሃ ግብርህ/ሽ ( ስኬጁል)ከአካዳሚያዊ ፍላጎቶችህ/ሽ ጋር እንደምስማማ ለማረጋገጥ ከአማካሪዎ ጋር ምክክር ያድርጉ። ለወታደራዊ አካዳሚ ፍላጎት ካለህ/ሽ ስለ ፍላጎትሽ/ህ አሁን መነጋገር ጀምር/ሪ። | ስኬጁልህ/ሽ አካዳሚያዊ ፍላጎቶችህ/ሽን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ከአማካርህ/ሽ ጋር ተወያይ/ይ። በ11ነኛ ክፍል ስፕሪንግ ወቅት ከአማካርህ/ሽ ጋርና ከቤተሰቦችህ/ሽ ጋር ስለ ኮላጅ እና ሌሎች የድህረ ሁለተኛ ደረጃ አማራጮች ያላችሁን ሃሳብ ተወያዩ። | የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ዕቅድህን/ሽን እና ለመግባት ከምታስበው/ስቢው የኮሌጆች ዝርዝር ጋር ለመገምገም ከአማካሪህ/ሽ ጋር ተገናኝ/ኚ።<br>ዝግጁና ንቁ ሁን/ኚ የቀነቀጠሮ ገደብ ቀኖችን እወቅ/ቂ የ FAFSA የመለያ ቁጥር አካዉንት ፍጠሪ/ር |
| ፍላጎትህ/ሽ ላይ የተመሰረተና እና ተገቢ የአካዳሚክ ደረጃዎችን በመምረጥ የ 4 ዓመት ዕቅድ አዉጣ/ጪ የተቻለዉን ምርጥ ዉጤቶችን ለማግኘት ጣር/ሪ | የአራት-ዓመት እቅድህን/ሽን አሻሽል/ይ እና የምትችለውን/ዉን ምርጥ ውጤት ማግኘትህን/ሽን ቀጥል/ይ. | ጥብቅ የሆኑትን ኮርሶችን መዉሰድና እንደዘሁም በተቻለ መጠን ምርጥ ዉጤቶችን ማግኘትህን/ሽን ቀጥል/ይ።<br>Naviance የምባለዉን ድረገጽ በመጠቀም ስለ ዋና ዋና ኮርሶች, ኮሌጆችና ፕሮግራሞች ተማር/ሪ።ለአትሌቶች የአትሌቶች ማጣሪያ/ መመልመያ ማዕከል በሆነው በ(NCAA) ወይም ለአንዳንድ የአነስተኛ ስፖርት ማእከሎች እንደ NAIA ባሉት መመዝገብን አስቢበት/በት | በተቻለህ/ሽ መጠን የተሻለ ውጤት ማግኘትህን/ሽን ቀጥል/ይ<br>በፎል ወቅት ለኮሌጆች ማመልከቻ ማስገባትን ጀምሪ/ር እንደዝሁም የትምህርት ትራንስክርፕት እና የድጋፍ ደብዳቤዎች ወደ መረጥከው/ሽው ኮሌጆች እንዲላክልህ/ሽ ጠይቅ/ቂ ። ስለ የድጋፍ ደብዳቤዎች መምህራንህን/ሽን ማስታወስ ያስፋልግሃል/ሻል<br>ለነጻ የትምህርት ዕድሎች እና ለ FAFSA እና / ወይም CSS ወይንም የኮላጅ የስኮላርሽፕ አገልግሎት በኦክቶበር ወር ዉስጥ ማመልከት ካስፈለገ ማመልከቻ አስገቡ ። |
| ተሳትፎ ይኑርህ /ሽ!<br>ክለብ ወይም ስፖርት ዉስጥ ተሳተፍ/ፊ | ተሳተፊ/ፍ እንድሁም ለዉጥ አሳይ/ይ የነጻ አገልግሎት ስጥ/ጭ ወይንም የነጻ አገልግሎት በምሰጡት ፕሮጀክት ውስጥ ተሳተፍ/ፊ. | በምትወደው/ጅው ክበቦች ወይም ስፖርት ውስጥ የአመራር ቦታ ዉሰድ/ጅ. | አመራርሽን/ህን ወደ ቀጣዩ ደረጃ በመዉሰድ የክለብሽ/ህ ወይንም የስፖርት ቡድን ፕሬዚዳንት ሁን/ኚ |
| ACT Aspire 9 እና PSAT 9 የምባሉትን ፈተናዎችን ውሰድ/ጂ | PSAT 10 እና Pre-ACT የምባለዉን ምዘናዎችን ዉሰድ/ጅ | የPSAT / NMSQT, SAT, ACT ይውሰዱ(SAT) እና የ SAT ወይንም የተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ፈተናዎችን ዉሰድ/ጅ ( አስፋላጊ ከሆነ) | በ12ተኛ ክፍል መጀመርያ ላይ ተጨማሪ የ ACT, SAT ወይም SAT ፈተናዎችን ውሰድ/ጅ። |
| የሰመር ጊዜ በፍቃደኝነት እና በአንዳንድ ፕሮጀክት ውስጥ በመሳተፍ ጊዜዉን ተጠቃሚ/ም ማንኛዉም የወደቅከበትን /የወደቅሽበትን የትምህርት አይነቶች በሰመር ወቅት አካክስ/ሽ ። | የኮሌጅ ማስተወወቅያ ፕሮግራሞችን ተካፈል/ይ የኮሌጅ ካምፓሶችን ጎብኚ/ኝ ፤ ስለ ኮሌጅ ትምህርትህ/ሽ የገንዘብ ጉዳይን በተመለከተ ውይይቶችን ይጀምሩ። | የኮሌጅ ማስተዋወቅያ ፕሮግሞች ላይ ተገኝ/ኚ ፤ ካምፓስን ጎበኝ/ኚ ምን ያህል ገንዘብ እንደምያስፈልግህ/ገምት/ቺ እንደዝሁም የስኮላርሽፕ ማመልከቻ ዕቅድህን አሰነዳ/ጅ ። | ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ቃለ-ምልልስ የምያስፈልግ ከሆነ አስቀድመህ/ሽ አቅድ/ጅ<br>የቅበላ ውሳኔ ከገኘህ/ሽ ቦሃላ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ ከመድረስህ/ሽ በፍት የመጀመርያ ምርጫሽ/ህ የሆኑትን 2-3 ኮሌጆችን ለመጎብኘት ዕቅድ አዉጣ/ጪ. |
| | የሰመር ጊዜን በሥራ፤ወይንም የነጻ አገልግሎቶችን በመስጠት ጊዜዉን ተጠቃሚ/ምእንደዝሁም ማንኛዉም የወደቅክበትን /የወደቅሽበትን የትምህርት አይነቶች በሰመር ወቅት አካክስ/ሽ | ከወላጅ (ጆችህ/ሽ) ከአሳዳጊህ/ሽ / አማካሪህ/ሽ ጋር በ11ኛ ክፍል ስብሰባ ላይ ተሳተፍ/ፊ ።<br>ከሰመር ዕረፍት በፊት ለኮሌጅ የድጋፍ ደብዳቤ እንድጽፉልህ/ሽ መምህራንህን/ሽን መጠየቅን አስቢበት/በት ። | የመግቢያ/የቅበላ ውሳኔዎችህን/ሽን ለአማካሪሽ/ህ አካፍለው/ይው እንደዝሁም ከዝህ ቦሃላ የምያታገኘዉንም /ዉንም ስኮላርሽፖችንም ተከታታል። ተጠባባቂ ከሆንሽ/ክ በንቃት ተከታታይ/ታል።<br>በሜይ 1 ወይም ከዚያ በፊት የኮሌጅ ምርጫ ዉሳኔህን/ሽን ለኮሌጁ አስተዳዳር አስተዉቃቸው።<br>ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመረቅ/ቂ! |
| | | ሥራ በመስራት ገንዘብን በማጠራቀምና እንደዝሁም የወደቅክበትን/ሽን የትምህርት አይነት ለማካካስ የሰመር የዕረፍት ጊዜውን ተጠቀምበት። | ሥራ በመስራት ገንዘብን በማጠራቀም የሰመር የዕረፍት ጊዜውን ተጠቀምበት።<br>የኮሌጅህን/ሽን አካዴሚያዊ ካለንደር እወቅ/ቂ እንደዝሁም ጉዞህን/ሽንና ዶርም ለመግባት አቅድ/ጂ . |

# የገንዘብ ድጎማ /ድጋፍ

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኃላ የትምህርት ፋይናንስን በተመለከተ ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ጭንቀት፤ ግንዛቤን ማግኘትና ጊዜን የምጨርስ ነገር ነው። ይህ እንደዝህ መሆን የለበትም ።አስቀድመው ከቀዱበት ጥሩ ልምድ ሊኖርዎት ይችላል። አሁን የምለፋበት ነገር ቦሃላ ላይ ፍሬ ያፈራል።

## ጠቃሚ ምክሮች:

- ስለ የገንዘብ አቅም ከቤተሰብህ/ሽ ጋር ቶሎ ውይይቶችን ጀምር/ሪ .
- ስለ ጠቅላላ ወጪዎች ግንዛቤ ይኖርዎት (በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የገንዘብ ድጋፍ ገጽ ላይ የምገኙትን ጠቅላላ ዋጋ(Net Price) የምባለዉን አስልዎች ይጠቀሙ።
- ስለ የገንዘብ ድጎማ ምንጮች ምርምር ያድርጉ
- የእስኮላርሽፖችን ዝርዝሮች እነ ተዘመዝጆችህን/ሽን ለማወቅ Naviance የምባለዉን ድረገጽ ተጠቀሚ/ም
- የጊዜ ገደብን ለመፈጸም ወደ ኋላ ዕቅድ ያውጡ
- ያመልክቱ! ማመልከትዎን ይቀጥሉ

## የእርዳታ/የገንዘብ ድጎማ ዓይነቶች-:

(በ12ተኛ ክፍል መጀመርያ አመት አክቶበር 1 ላይ FAFSA የምባለዉን የፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ እርዳታ የሆነዉን ማመልከቻ ይሙሉ።

- የFAFSAን ማመልከቻ በማስገባት (EFC)ወይንም የቤተሰባችው የገንዘብ ድርሻ በግምት ምን ያህል እንደሆነ ይወሰናል። (EFC) የቤተሰብዎን የገንዘብ አቅም በህጋዊ አሠራር ላይ በመመስረት ይመዝናል።. EFC ወይንም የቤተሰብዎ የገንዘብ ድርሻ በግምት የምባለው የተማሪዎች ቤተሰብ መክፈል ያለበት የገንዘብ መጠን አይደለም።ተማሪዎች ምን ያህል የገንዘብ ዕርዳታን ለመቀበል ብቁ እንደሆኑ ለመለካት በኮሌጅ / ዩኒቨርሲቲዎ ጥቅም ላይ የሚውል መጠን ነው.
- የፌደራል መንግሥት ( Pell)ፔል የምባለዉን የገንዘብ ድጋፍ እና እንደዝሁም ተማሪዎች ግማሽ ጊዜ( ፓርትታይም) ሥራ እያሰሩ እንድማሩ ድጋፍ ማድረግ ይችላል። እነዚህ ሽልማቶች/ድጋፎች የምሰጡት በፌደራል መንግሥት የምወሰንና አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች ነው ። ለዝህ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ መሆንህን/ሽን ለማረጋጋጥ FAFSA የምባለዉን ማመልከቻ ማስገባት አለብህ/ሽ ። FAFSA ማለት ተማሪዎች ከፌደራል መንግስት የገንዘብ ድጋፍን ለማግኘት የምጠቀሙበት ነጻ ማመልከቻ ነው። ማመልካቸዉ በዝህ ድረገጽ ላይ ይገኛል። **www.fafsa.ed.gov**.

## የተቋማዊ እገዛ

- አብዛኛዎቹ ኮሌጆች / ዩኒቨርሲቲዎች በቀጥታ ለተቋማቸው በምገባ ማመልከቻዎች መሰረት ለተማሪዎች የምሰጡት የነጻ የትምህርት ዕድሎችና የገንዘብ እርዳታዎች አሏቸው። እነዚህ የገንዘብ ድጋፎች (በተማሪዎች ከፍተኛ አካዴሚያዊ ብቃት ) ወይም አነስተኛ የገንዘብ አቅም ላይ የተመረኮዘ ልሆን ይችላል እንደዝሁም አብዛኛውን ጊዜ የጊዜ ገደብ እና ሌሎች መስፈርቶችም አላቸው.
- አንዳንድ የግል ኮሌጆች / ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች FAFSA ከምባለው ማመልከቻ በተጨማሪ የኮሌጅ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም ወይንም (CSS) የምባለዉን ማመልከቻ እንዲሞሉ ይፈልጋሉ። ይህ ማመልከቻ በ12ተኛ ክፍል የትምህርት ጊዜህ/ሽ አክቶበር 1 ላይ ይለቀቀል።
  The የCSS ወይንም የኮለጅ ስኮላርሽፕ ማመልከቻ ፕሮግራም በዝህ ድረገጽ ላይ ይገኛል **https://cssprofile.collegeboard.org/**.
- በተጨማሪ ለየት ያለ ትግበራ ሊጠይቁ ለሚችሉት ተጨማሪ ነጻ የትምህርት እድሎች የኮለጆቹን የገንዘብ ድጋፍ ሰጪ ድረገጾቹን ተከታታል/ይ

### የገንዘብ ስጦታዎች

- ግራንት የምባሉት የገንዘብ ስጦታዎች ለሰጪው የማይመለሱና በስጦታ መልክ የምሰጥ ገንዘብ ነው ።ይህ የገንዘብ ስጦታ በፌዴራል መንግስት, በስቴት መንግሥታት, በኮሌጆች እና በዩኒቨርሲቲዎች ልሰጡ ይችላል እንደዝሁም ከተለያዩ ኩባንያዎች፤ ተቋማት እና ድርጅቶች ሊመጡ ይችላሉ።
  የPell Grant የምባለውን ስጦታ የመቀበል መስፈርቱ የምወሰነው (FAFSA) በምበለው ነጻ ማመልከቻ ላይ በቀረቡት መረጃ መሰረት ነው። ምንም እንኳን ገንዘብ ለመበደር ዕቅድ ባይኖርህም/ሽም ምን ዓይነት የገንዘብ ዕርዳታ ሊያገኙ ይችሉ እንደሆነ ለማየት የFAFSA ማመልከቻ ያስገቡ።


### የግል( የበጎ አድራጎት) ስኮላርሽፕች

- ስኮላርሽፖች ብዙውን ጊዜ የምሰጡት በትምህርት ዉጤት ላይ በመመስረት ስሆን በምሰጠው የገንዘብ መጠን, በማመልከቻዉ የማስገቢያ ቀነ ቀጠሮ፤ እና በማመልከቻ መስፈርቶች አንፃር ይለያያሉ ።አካዴሚያዊ ስኮላርሽፕች በተለምዶ ብዙውን ጊዜ በጥራት ላይ የተመሠረተ ወይንም ከፍተኛ ዉጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች የምሰጥ የነፃ ትምህርት ዕድል ተደርገው ይቆጠራሉ። የግል ስኮላርሽፖች በተለያዩ ብዙ ድርጅቶች ልሰጡ ይችላሉ።. የገንዘብ ድጋፍ ልሰጡ የምችሉትን በአካባቢዎ ያሉትን ባንኮችን, ድርጅቶችን እና ማህበረሰባዊ ድርጅቶችን እነ አሰሪዎችን ያጥኑ
- ከአንዳንድ አካዳሚዎች ስኮላርሽፖች ውጪ, አንዳንድ አትሌቶች የትምህርት ቤት ወጪን ለመሸፈን የሚረዱ ሙሉ ወይም በከፊል የአትሌትክስ ሽልማትን ያገኛሉ.

## የተማሪ እና የወላጅ ብድሮች( የአራጣ ብድሮች)

- ለገንዘብ እርዳታ የሚያመለክቱ ከሆነ, እንደ የገንዘብ ድጋፍ ዕቅዶች አካል በመሆን, የተማሪ እና የወላጅ ብድርም ሊሰጥዎት ይችላል. የተማሪ እና የወላጅ ብድሮች ተማሪው/ዋ የድግሪ ትምህርቱን/ቷን ከተጠናቀቀ/ች በኃላ ወይም ትምህርቷን/ቱን ከቆመ/ች ቦሃላ በየጊዜው ከነወለዱ መከፈል ያለባቸው የገንዘብ እርዳታ ናቸው። ብድሮች በአካባቢዎ በሉት የገንዘብ ተቋማት, በፌደራል መንግስት ወይም በግል አባዳሪዎች ልሰጡ ይችላሉ። በፌደራል የምሰጥ (ዋስትና ያለቸው የተማሪ ብድሮች) እና የወላጅ (ተጨማሪ ብድር) በአጠቃላይ የወለድ ተመኖቻቸው ዝቅተኛ ነቸው።

ለኮሌጅ የምያስፈልጋችሁን የገንዘብ መጠንን ለመወሰን ከዚህ በታች ያለውን መሠረታዊ ቀመር/ፎርሙላ ይጠቀሙ። ለኮሌጅ የምያስፈልገዉን ጠቅላላ ወጪና የቤተሰብ የገንዘብ አቅም/ድርሻ ከወቅሽ/ክ የብቁነትህን/ሽን ደረጃ መወሰን ትችላለህ/ያለሽ ። የብቁነት መጠን የምባለው በቤተሰብ መዋጮ፤ በስኮላርሺፕ እርዳታ እና ብድር እንድታሟሉት ኮለጆች የምረዱቸው ማለት ነው።



# የምክር አገልግሎቶች




የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ( በከፍተኛ ደረጃና መከከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቃት ያላቸዉን አማካሪ ባለሙያዎችን በመቅጠሩ ኩራት ይሰማዋል እያንዳንዱ መካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት / ቤት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለምሳሌ የትምህርት ነክ ፤ማህበራዊ፤ስሜታዊ ወይንም ለስራና ኮሌጅ ዝግጁነት ጉዳይ ላይ ተማሪዎችን ለመርዳት ብቁና ዝግጁ የሆኑ የቡድን እና የተቀናጀ የምክር ኣገልግሎት የምሰጡ ትጉ አማካሪዎች አሏቸው።

. የትምህርት ቤት አማካሪዎች አዎንታዊውን የትምህርት ቤት ባህልን ለመገንባትና ለመደገፍ  እና ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቦሃላ ያለዉን  እቅድ ለማውጣትም ተማሪዎችን  ልረዱ ይችላሉ።

## የአማካሪዎች ሥራ  ምንድነው?

የት / ቤት አማካሪዎች ቢያንስ የማስትሬት ድግሪ ያላቸዉና  በተላይ ለዝህ ሥራ የሰለጠኑ በሚከተሉት ሶስት ጎራዎች ውስጥ ማለትም አካዳማዊ ፤ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና የሙያ ስራ / የኮለጅ እቅድ ማዉጣትን ጨምሮ  ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ አገልግሎቶችን በማቅረብ ተማሪዎችን  ለመደገፍ ልዩ ብቃት ያላቸው  ባለሞያዎች ናቸው። በትም / ቤት አማካሪዎች አመራር፤ ትብብር እና አማካሪነት፤ ፍትሃዊነት እና ጥብቅ አካዳሚካዊ ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ ተደርጓል።

ከተማሪ እና ከቤተሰብ ድጋፍ በተጨማሪ፤ አማካሪዎች ከት / ቤት ሰአት  በኋላ ቡድኖችን /ክላቦችን  ማስተባባር፤ መረጃን መሰበሳብና መመርመር ይችላሉ። እንድሁም ከኮሌጅ እና ሙያ ባለሞያዎች ጋር በመተባበር የማህበረሰብ ግንኙነትን ማጎልበት፤ ለአእምሮ ጤና ቡድኖች በአመራር ደረጃ ዕገዛን መስጠት ወይም በድስትሪክቱ ዉስጥ በምገኙት ኮሚቴዎች ዉስጥ  በፈቃደኝነት  ማገልጋል ይችላሉ። በተጨማሪም አማካሪዎ የተማሪዎች የ504 ጉዳይ አስፈጻሚ   ስለ (ALP)ወይንም ከፍተኛ የመማር ዕቅድ  በምባለው ስብሰባዎች ላይ ማማከር እና የግል የትምህርት እቅድ (IEP) ሊኖራቸው የሚችሉ ተማሪዎችን ለመደገፍ በስብሰባዎች ውስጥ ይገኛሉ.

## ከአማካሪዬ ጋር መገናኘት  ያለብኝ መቼ ነው?

የምክር መስጫ ሞዴሎች ከት / ቤት  ት / ቤት ይለያያሉ።አንዳንድ የመማክርት ቡድኖች የአልፋ ማለትም የተማሪዎችን  ስም/የአያት ስም የመጀመርያውን  ፍዳል የመጠቀም ሞዴሎችን ይመርጣሉ, ሌሎች ደግሞ የክፍል ደረጃን ሞዴል ይጠቀማሉ የተማሪውን ብዛት  ፍላጎቶች ለማሟላት ሁለቱንም  ሞዴል ይመርጣሉ።ለትምህርት፤ ለማህበራዊ-ስሜታዊ እና ለስራ / የኮላጅ ፍላጎቶችህ/ሽ ድጋፍ ለማድረግ የተመደበ አማካሪ አለህ/ሽ። አማካሪዎች የተማሪዎችን ፍላጎቶች  ለማሟላት ዘረፈ ብዙ ካሪኩለም ነድፈዋል: ቀጥተኛ  አንድ ለአንድ ፤ ስብሰባዎች፤ትንሽ እና / ወይም ትልቅ ቡድን ስብሰባዎች የክፍል ስብሰባዎች ወይም ቀጥተኛ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል። በትምህርት ቤት ቆይታችው ወቅት ከአማካሪዎቻችው ጋር ለመገነኘት የተመደቡ ቀናት/ሰአቶች ይኖሯቸዋል። ሆኖም ግን  ስጋት ወይንም የምትፈልገው/ጊው ነገር ካለህ/ሽ  ከአማካሪህ/ሽ ጋር ለመነጋገር ጊዜ ቀጠሮ ያዝ/ዥ።



# የትምህርት ቤቶቻችን ምደባ( የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች)

| ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | መከከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
|---|---|
| Cherokee Trail | Fox Ridge |
| | Sky Vista* |
| | Thunder Ridge* |
| Cherry Creek | Campus |
| | West |
| Eaglecrest | Horizon* |
| | Thunder Ridge* |
| | Sky Vista* |
| | Infinity |
| Endeavor | ሁሉም የመከከለኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች |
| Grandview | Falcon Creek |
| | Liberty |
| Overland | Prairie |
| Smoky Hill | Horizon* |
| | Laredo |

የቼሪ ክሪክ አካዳሚ (ቻርተር) እና የቻለንጅ ትምህርት ቤት ተማሪዎች (K-8) ወደ ቤታቸው አድራሻ ባለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይመደባሉ School.የHorizon, የSky Vista እና የThunder Ridge መካካለኛ ደረጃ ት / ቤቶች ተማሪዎች በእያንዳንዱ ተማሪ የቤት አድራሻ መሰረት ወደ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይመዳባሉ፡፤

# የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ቢሮዎች አድራሻ/ስልክ

| | |
|---|---|
| የEast በኩል የምዝገባ አድራሻ | 720-886-7480 |
| የ West በኩል የምዝገባ አድራሻ | 720-554-4550 |
| የዲስትሪክት አማካሪ አስተባባሪ | 720-554-5090 |
| የትምህርት ክንዋኔዎች | |
| አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | 720-554-4215 |
| መከከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | 720-554-4209 |
| ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | 720-554-4287 |
| የግምገማ እና የምዘናዎች ቢሮ | 720-554-5001 |
| የአዕምሮ ጤንነት ቢሮ | 720-554-4259 |
| የተማሪ ስኬት አገልግሎቶች | 720-554-4236 |
| የከፍተኛ አካዳሚክ አገልግሎቶች | 720-554-5052 |

Dedicated to Excellence
Cherry Creek Schools